


# የዩኤስ ለአካለ መጠን ላልደረሱ የሚሰጡ ፓስፖርቶች

### ዕድሜያቸው 15 ዓመትና ከዚያ በታች ለሆኑ

## የፓስፖርት ደብተርና የፓስፖርት ካርድ

- የፓስፖርት ደብተር የሚያገለግለው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በአየር፣ በየብስና በባህር ሲገቡ ይሆናል።
- የፓስፖርት ካርድ የሚያገለግለው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በየብስና በባህር ሲገቡ ብቻ ነው፤ ሆኖም ግን ለዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ አያገለግልም።
- የፓስፖርት ካርድ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በየብስ ኬላ ጣቢያዎች ባሉ ዝግጁ በሆኑ የመግቢያ መስመሮች ሲገቡ ሊገለገሉበት ይችላሉ።
- ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች ለሆኑ የሚሰጠው ፓስፖርት የሚያገለግለው ለ5 ዓመት ነው።
- የፓስፖርት ካርድ መጠኑ የክሬዲት ካርድን ያክላል ስለሆነም እንደመታወቂያም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።
- ደብተሩንና ካርዱን በአንድ ግዜ ለማግኘት ማመልከት ወጪን ይቀንሳል።

## ለልጅ ፓስፖርት ለማመልከት የሚያስፈልግዎ:-

- ዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ መሆንዎን ማረጋገጫ፤ ለምሳሌ እንደ ዩናይትድ ስቴትስ የልደት ምስክር ወረቀት።
- ወላጆች ወይም ህጋዊ ሞግዚቶች ፎቶግራፍ ያለበት በመንግስት የተሰጠ የሚሰራ ለምሳሌ እንደ መንጃ ፈቃድ፣ በስቴቱ የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ወይም የአሜሪካ ወይም የሌሎች አገሮች ፓስፖርት ማቅረብ አለባቸው።
- ወላጆች ወይም ህጋዊ ሞግዚቶችና ልጁ ወይም ልጅቷ በአካል መቅረብ አለባቸው።
- ምናልባት አንደኛው ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት በአካል መቅረብ ካልቻለ የተረጋገጠ የፅሁፍ ስምምነት (ፎርም DS-3053) አሟልቶ ማቅረብ ያስፈልጋል።
- አንድ መጠኑ 2”x2” የሆነ የቀለም ፎቶ።
- የፓስፖርት ማመልከቻ DS-11.
- የፓስፖርት ክፍያ።

## ለተጨማሪ መረጃ

1-877-487-2778 (እንግሊዘኛና ስፓኒሽ)
ወይም 1-877-874-7793 TDD/TTY
travel.state.gov/passports